ECIC
የጀግኖች … .የአናብስት መንደር
የቅድስት ኢትዮጵያ ወጣቶች ሰፈር
ጋንጩርን ለመፋለም በቁርጠኝነት የተነሱ
የዘመኑን ቴክኖሎጂ እውቀትን የለበሱ

ECIC .
የመናፍቃን የእውን ….ቅዥት
አልተው ያላቸው … ራስ ምታት
ማስመስያ ጭንብላቸውን አውልቆ
በጥቅስ የተሸፈነውን ደባ ፈልቅቆ
እውነቱን አደባባይ ያወጣ
የአምታታኞቹ ፓስተሮች …ባላንጣ
በመተዳደርያቸው ….የመጣ

ECIC
አከተመ …አላቸው
ለጴንጤው ፓስተሮች
በምላስ ካራቴ … በቃላት አክሮባት
በጥቅስ በታጀቡ .. የተዋቡ ቃላት
… ድምጽን አለስልሶ
… አንገት አቅለስልሶ
በክርስቶስ ስም የዋሑን መደለል
ገንዘብ መመዝበሩ በእምነት ማታለል

ECIC
አበቃ !! ..አላቸው … ለእነቁጭ በሉ
አትችሉም ከእንግዲህ .. ሰው ልታታልሉ

ማስረጃዎቹን ይዞ ECIC መጣ
እውነቱን አደባባይ ገሐድ እያወጣ
የአምታታኞቹ ፓስተሮች … የእነ ቁጭ ይበሉ ባላንጣ

ECIC
የጀግኖች ….የአናብስት መንደር
የቅድስት ኢትዮጵያ ወጣቶች ሰፈር
ጋንጩርን ለመፋለም በቁርጠኝነት የተነሱ
የዘመኑን ቴክኖሎጂ እውቀት የለበሱ

ECIC
የመናፍቃኑን ፓስተሮች
… የእነ ቁጭ በሉን

ገፈፈ የበግ ለምዳቸውን
አደባባይ አውጣ ተኩላነታቸውን

ECIC
ጋንጩርን ለመፋለም .. ቆርጦ የተነሱት
የቅድስት ኢትዮጵያ አናብስት
የዘመኑን ቴክኖሎጂ የተካኑት
እነ ባራንባራስ : እነ ምረድ : እነ ደልፊን
ይሄው ... ዋርካ ላይ ምድረ መናፍቁን ያንጫጩታል
የሐሰት ግንብ የእንቧይ ካቡን ...ደረማምሰው ጥለውታል

እኛም አበጀህ ... ይበል ...ብለናል
በ ECIC .... እጅጉን ኮርተናል
ከምስጋና ጋር ... ብዙ ተምረናል !!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!

__________________
http://www.ethiopianorthodox.org/

http://www.saveethiopians.net/